# <u>የትምህርት ነገር</u>
## "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ"

ኢህአዴግ የምርጫ - 2002 ዘመቻውን ጀምሯል፡፡ የአሁኑ ዘመቻው ከምርጫ 97ቱ የሚለየው ያለተፎካካሪ ብቻውን እየሮጠ ያለ በመኾኑ ነው፡፡ በምርጫ 97 ዘመቻ ወቅት በአንድ በኩል የቅንጅት እና የኅብረት መሪዎች፣ በሌላ በኩል ከአቶ መለስ በስተቀር አሉ የሚባሉት የኢህአዴግ መሪዎች ተሳታፊዎች ነበሩ:: ሌሎቹ ለምርጫው በተደረገው ፉክክር ትርፍ ሰላላመጡ ነው መሰለኝ፣ አሁን አቶ መለስ ብቻ ነው ዘመቻው ውስጥ ያለው፡፡ በሌላ አንጻር ተሰልፈው የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተገዳዳሪዎችም ዛሬ የሉም፡፡ ኢህአዴግ የፉክክር ሜዳውን ለብቻው ሲሮጥበት በሌላ በኩል ደግሞ የወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን በድጋሚ መታሰር፤ ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲ እና ለሉአላዊነት ፓርቲ በመቀሌ ከተማ ሕዝባዊ ስብሰባ ለመጥራት ያጋጠመውን ችግር እንዲሁም ‹‹አንድነት›› ለዴሞክራሲ እና ለፍትሕ ፓርቱ የሥነ ጽሑፍ ምሽት ለመጥራት እንኳ ፈቃድ መከልከሉን ልብ ይሏል፡፡

ሰሞኑን አቶ መለስ ሥራ በዝቶበታል፡፡ ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ፣ ‹‹ከሰባት ሺሕ ያላነሱ›› ወጣቶችን ሰብስቦ አነጋግሯል፤ ቅዳሜ የካቲት 21 ቀን በሃድያ ዞን የዩኑቨርሲቲ የመሰረት ድንጋይ አኑሮ፣ ከምባታ ጠንባሮ ዞን ላይ ታይቶ፣ እሁድ የካቲት 22 ቀን ደግሞ ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ ናቸው የተባሉ ሦስት ሺሕ መምህራንን ሲያወያይ ውሏል፡፡ በ‹‹ማርች ስምንት››ም ከሴቶች ጋራ እንዲሁ ሌላ ስብሰባ ይኖራል እየተባለ ይወራል፡፡ በዚህ ስሌት በ‹‹ሜይ ዴይ›› በዓልም ከሠራተኞች ጋራ ተመሳሳይ ውይይት ይደረግ ይኾናል፡፡

ከመምህራን ጋር የተካሄደው ስብሰባ በምርጫ 97 ወቅት የነበረውን ኹኔታ ነው ያስታወሰኝ፡፡ በምርጫ ፉክክሩ የኋላ ጊዜ በተካሄዱት አብዛኛዎቹ የፖሊሲ ክርክሮች ኢህአዴግ ‹‹በአዳራሹ የሚገኙት ሰዎች ቁጥር ይወሰንልኝ›› ባይል ኖሮ ክርክሩ በሚካሄድበት አደራሽ ለመሰብሰብ የሚፈልገው ሰው በጣም ብዙ ነበር፤ ገደብ ተደርጎም ቢኾን ክርክሩን ወደ አዳራሽ ገብቶ ለመከታተል የሚሻው ሰው በርካታ ነበር፡፡ ገደብ ተደርጎም ቢኾን በሬድዮና በቴሌቪዝን በቀጥታ ይሰራጭ የነበረውን ክርክር ሕዝቡ ይከታተል የነበረው በታላቅ ጉጉት እና በራስ ተነሣሽነት መንፈስ ነበር ፡፡

የእሑዱ የመምህራን ስብሰባ በቴሌቪዥን እና በሬድዮ በቀጥታ የተሰራጨ ቢሆንም አስተማሪዎቹ ጭምር ውይይቱን የመከታተል ፍላጎት እንደማይኖራቸው ስለተገመተ ቴሌቪዥን እንደልብ በሚገኝበት አዲስአበባ ሳይቀር መምህራን በየትምህርት ቤታቸው ቅጽር ግቢ ተገኝተው ሥርጭቱን በፕላዝማ ቴሌዥን እንዲከታተሉ ትእዛዝ ወርዶባቸዋል፤ እሑድ ሰንበት እንደ ሥራ ቀን ተቆጥሮ የተለመደው ምዝገባና ቁጥጥር እንደሚካሄድም ተነግሯቸዋል፡፡

ምርጫ 97 ላይ ለክርክሩ የመጀመሪያው አጀንዳ እንዲኾን የተመረጠው የትምህርት ፖሊሲው ሲሆን በዚሁ ጉዳይ ኢህአዴግን ወክለው ለክርክሩ የቀረቡት አቶ ተፈራ ዋልዋ እና ወ/ሮ ገነት ዘውዴ ነበሩ፡፡ በወቅቱ ‹‹ኢህአዴግ ትልቅ ለውጥ አመጥቸበታለኹ›› ብሎ የሚናገርለት ዘርፍ ትምህርት በመሆኑ በዚህ ዙሪያ በሚደረግ ክርክር የበለጠ ትርፍ አገኝበታለኹ ብሎ ሳይገምት አልቀረም፡፡ በክርክሩ ሂደት ኢህአዴግ ሥርጭቱ ላይ በማተኮር በኢትዮጵያ የትምህርት ሽፋን ምን ያህል እንደተስፋፋ ለማሳየት በደርግ ዘመን የነበረውን የትምህርት ሽፋን ለማነጻጸርያነት ማቅረቡ አልበቃ ስላለው ከዐፄው ጊዜ እየተነሳ የተገኘውን ለውጥ ሲገልፅ ነበር፡፡ ተቃዋሚዎች ግን ፖሊሲው ባሉት ዉሱንነቶች፣ ፖሊሲው ባስከተለው እና ሊያስከትል በሚችለው ችግር

ላይ ነበር ያተኮሩት፡፡ በወቅቱ ተቃዋሚዎች አጽንኦት ሰጥተው ከተከራከሩባቸው ችግሮች ሌላው እና ትልቁ የጥራት ችግር ነበር፡፡ ኢሕአዴግ በበኩሉ ‹‹*በስርጭት ለተገኘው ስኬት እንኳን እውቅና የማትሰጡ፣ ከመቃወም በቀር ሌላ የማታውቁ*› ብሎ ነበር ተቃዋሚዎቹን የተቻቸው፡፡

ከአራት ዓመት በኋላ ባለፈው ሳምንት በተካሄደው በእሕዱ ስብሰባ ላይ ግን አቶ መለስ ሲናገር የትምህርት ጥራት ችግር ‹‹*አጣዳፊ*›› እና ‹‹*ትልቁ የትምህርት ጉዳይ*›› በሚሉ ቅጽሎች ገልፆታል፡፡ ተቃዋሚዎች ከአራት አመት በፊት ያሉትን እውነታ ለመገንዘብ ኢህአዴግ ይህን ያክል ጊዜ የወሰደበት ለምን ይሆን? አሁንስ ኢህአዴግ ይህንን ችግር በውል ተገንዝቦት ነው እየተነጋገረበት ያለው? ወይስ በዚሁ ዙሪያ ሊነሱ ለሚችሉት ጥያቄዎች ‹‹ችግሩን ተገንዝቤዋለሁ መፍትሄም አስቀምጨለታለሁ ብሎ›› አቋራጭ መልስ ለመስጠት እንዲመቸው ነው?

<u>"የአፈጻጸም እንጂ የፖሊሲ ችግር የለም"</u>

ኢህአዴግ በምርጫ 97 ላይ ከደረሰበት ውድቀት በኋላ ‹‹ግምገማ አካሄጃለሁ›› ይላል፤ በግምገማውም ደረስኩበት ያለው ግኝት ድርጅቱ "የአፈጻጸም ችግር እንጂ የፖሊሲ ችግር" እንደሌለበት ነው፡፡ ያኔም ቢሆን ተቃዋሚዎች ፖሊሲ እና አፈፃፀሙ ተነጣጥለው የሚታዩ ነገሮች አይደሉም፤ ፖሊሲ በመሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ እና የመስፈጸም አቅም መሰረት አድርጎ ካልተቀረፀ ‹‹የማይተገበር የወረቀት ፖሊሲ ነው›› ብለው ተከራክረው ነበር፡፡ ኢህአዴግ የጥራት ችግር አጣዳፊ እና ትልቁ የትምህርት እንከን መሆኑን ቢገልጽም መምህራኑን ለስብሰባ የጠራቸው ግን በችግሩ ምንጭ እና በመፍትሄው ፍለጋ ዙሪያ እንዲመክሩ አይደለም፡፡

ችግሩ የጥራት መሆኑን ‹‹ደርሼበታለሁ›› ከማለቱ በቀር የችግሩ ምንጭ ምን እንደሆነ ለመግለጽ እና በዚሁ ዙሪያ ለመመካከር አልመጣም፤ አስተማሪዎቹን የጠራቸው "ችግሩ የጥራት ነው" በተባለው ጉዳይ ላይ ተወያይተው መፍተሄ የሚሉትን ለመጠቆምም አይደለም፡፡ በኢህአዴግ ቤት መፍትሄውም ታውቋል፤ ለዚሁም ‹‹ፓኬጅ›› እንደተዘጋጀለት ለአስተማሪዎቹ ተገልፆላቸዋል፡፡ እነሱ የተጠሩት ‹‹ችግሩን ይፈታል›› በሚል በፓኬጅ መልክ የተዘጋጀ ክኒን መኖሩን እንዲያውቁ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ መስማት ብቻውን በቂ ስለሆነ መምህራኑ ከግኡዙ የፕላዝማ ቴሌቪዥን ጋር እንዲፋጠጡ ተደረገ፡፡ ይህች ፓኬጅ የተባለች ክኒን ያልገባችበት ቦታ የለም፡፡ የግብርና ፓኬጅ፣ የወጣቶች ፓኬጅ፣ የሴቶች ፓኬጅ፣ ነገም ለሰራተኞች ፓኬጅ ተዘጋጀ ሲባል እንሰማ ይሆናል፡፡

ፖሊሲ እና አፈፃፀሙ የማይነጣጠሉ የመሆናቸው ጉዳይ ግልፅና የማያሻማ ሆኖ እያለ ኢህአዴግ ሁለቱን አጣምሮ ማየት ያልፈለገበትና ያልቻለበት ምክንያት ምንድነው? ፖሊሲ ከአፈፃፀሙ በመለየት ለየብቻ እንዲታይለት የሚፈልገውስ ለምንድነው? የሚሉት ጥያቄዎች በጥሞና መመርመርና መመለስ ያለባቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ናቸው እላለሁ፡፡

ችግሩ የፖሊሲ ነው ማለት በሌላ አነጋገር ችግሩ ኢህአዴግ የሚመራበት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካዊ መስመር ችግር ነው፤ ከዚሁም በተጨማሪ ችግሩ የድርጅቱ መሪ ብቃትም ነው ማለት ስለሚሆን፤ አቶ መለስ እና ኢህአዴግ ይህን ዐይነቱን ዕይታ አይፈልጉትም፡፡ ይልቁንም ከዚህ ለማምለጥ ሲሉ "ችግሩ የአፈፃፀም ነው" ይሉና ተጠያቂነቱን ከእነሱ ላይ ያርቁታል፤ መፍትሔውም ፖሊሲውንና እነሱን መፈተሽ እንዳይሆን ይሁነን ብለው "ፓኬጅ" በሚል ወደ ጠሩት ሁለገብ ክኒን ይመሩታል፡፡

በእኔ አስተያየት ችግሩ ያለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዘንድ ነው። በአገራችን ሁሉም ነገር ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እና ከኢህአዴግ ጋር ተያይዟል። ሁሉም ነገር ከአንድ ፓርቲ እና ከአንደ ዐምባገን አገዛዝ ጋር ተሳስሯል። ይህ አገዛዝ እና አመለካከት ከሚያየው ውጭ የሚያስቡ እና የሚመለከቱ ምሁራን ቢኖሩም የሚታያቸውን ለሚመለከተው በግልፅ ቢናሩ አባባላቸው ኢህአዴግን እና አብዮታዊ ዴሞክራሲን መቃወም ተደርጎ ሊወሰድባቸው ስለሚችል "የፈንጂ ወረዳ" ላለመግባት ሲሉ አለመናገርን ይመርጣሉ፤ መናገር ግድ ከኾነባቸውም ንግግራቸው ጭንቀት የተሞላበት ለመኾኑ በመድረኩ ከተሳተፉት አስተማሪዎች ኹኔታ ታይቷል። ከአራት አመት በኋላም እዛው ክርክሩ ከቆመበት ቦታ ላይ ራሳችንን ለማግኘታችን ምክንያቱ ይህ ነው።

<u>ያለ ነፃነት ትውልድ አይገነባም ትምህርትም አይጠራም</u>

አቶ መለስ ከወራት በፊት በዚሁ መምህራንን በሰበሰበበት አዳራሽ ውስጥ ከንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ጋር ስብሰባ አካሂዶ ነበር። የመምህራን ስብሰባው ከመካሄዱ ከሳምንታት ቀደም ብሎም በሚልየነሙ አዳራሽ የወጣቶች ስብሰባ ጠርቶ ነበር። በሁሉም ስብሰባዎች ላይ የሚታይ ተመሳሳይ ችግር አለ። ተናጋሪዎቹ ይኹኑ የሚናገሩት ጉዳይ አስቀድሞ የሚታወቅ ነበር የሚመስለው፤ ተናጋሪዎቹ እንዳይሳሳቱ እየተጨነቁ ያጠኑትን ንግግር የሚናገሩ ነበር የሚመስሉት። ለዚህ ዓይነቱ ጨዋታ ግን ለምን ይህን ሁሉ ገንዘብ እና ጊዜ እንደሚወጣ አይገባኝም። የኢህአዴግ ግብ ሕዝቡን ‹‹ማሳመን›› ከሆነ እና መሪዎቹም ለማሳመን እንችላለን የሚል ተኣምኖ ካላቸው ተሰብሳቢውን በነፃነት መንፈስ እንዲወያይ እና እንዲጠይቅ ይፍቀዱለት፤ ይህን ለማድረግ ካልፈቀዱ ደግሞ እንደለመዱት ጥያቄዎቹን ለጋዜጠኞቻቸው ያድሉ እና "ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ" በሚል መልኩ ይቅረብና የፈለገ ይስማው ያልፈለገ ደግሞ በገዛ ጊዜው የፈቀደውን ያድርግበት።

በሚሊየነሙ አዳራሽ የወጣቶቹ ስብሰባ በተካሄደበት ሰሞን ሌላ የወጣቶች ስብሰባ በብሄራዊ ቴኣትር አዳራሽ ተካሂዶ ነገር። ተሰብሳቢዎቹ የትግራይ ተወላጅ ወጣቶች ናቸው፤ ሰብሳቢው ግን አቶ መለስ ሳይኾን ሌላ የህ. ወ. ሓ. ት. ተወካይ ነገር። ብሔራዊ ትያትር ቤት ተውኔት ቢኾንም ስብሰባው ግን የሚሊንየም አዳራሹ ስብሰባ ባህርይ እንዳልነበረው ጋዜጦች አስነብበውናል። ወጣቶቹ የመሰላቸውን ጥያቄ አንስተዋል፣ ትችትና አስተያየታቸውንም ሰጥተዋል። የኢትዮጵያ ወጣቶች ድራማዊ ባልሆነ፤ ያለመልማይ እና ያለአስጠኚ በነፃነት ሲሰበሰቡ ምን አንደሚሉ እና ምን እንደሚጠይቁ ከብሄራዊ ትያትሩ ስብሰባ መገንዘብ ይቻላል። አቶ መለስ እና ኢህአዴግ ካደረጉ አይቀር ለዘመኑ ትውልድ እና ለመላ ኢትዮጵያውያን እንዲያዘጋጁለት የሚጠበቅባቸው መድረክ እንደዚህ ያለ ነጻ የሐሳብ ልውውጥና ክርክር የሰፈነበት ውይይት ነው። አቶ መለስ ይህንን ለማድረግ ፍላጎቱ እና ድፍረቱ ከሌለው በምርጫ 97 ላይ እንዳደረገው ከነአካቴው ለውይይት አለመቅረብ ይሻለዋል።

ፈሪ እና ተጠራጣሪ ዜጋ አገርን አይገነባም፤ ያለ ነፃነት ትውልድ አይገነባም፤ ያለነጻነት የትምህርት ሥርዓቱ ከገባበት ችግር ሊወጣ አይችልም። በኢትዮጵያ ከምር ለውጥን ለማምጣት ከተፈለገ የኢህአዴግ መንግስት የዐዬውና የመንግስቱ ኃ/ማርያም መንግስታት ከነበረባቸው ወጣቱንና ሙሁሩን የመፍራት በሽታ መውጣት አለበት። ተማሪዎችም ሆነ ትምህርታቸው ከፓርቲ ፖለቲካ ተጽዕኖ አርነት ወጥቶ በነጻነት መንፈስ እንዲጠይቁና እንዲተቹ የሚያስችላቸው ኹኔታ መመቻቸት አለበት። አስተማሪዎች በነፃነት መንፈስ እንዲያስቡ እና እንዲሠሩ፤ የራሳቸው ነጻ ሙያዊ ማኅበር እንዲኖራቸው መደረግ ይገባዋል። ኢህአዴግ የትምህርት ጉዳይ ሁሉንም

ኢትዮጵያውያን የሚመለከት ትልቅ የሃገር ጉዳይ እንጂ፤ የአንድ ፓርቲ ጉዳይ ብቻ አለመኾኑን ተቀብሎ ልዩነትን በሆደ ሰፊነት በማስተናገድ ለሃገር የሚበጀው በጋራ ጥረት ነጥሮ እንዲወጣ ሁኔታውን ማማቻቸት አለበት። በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ ይህ እውነታ እንደሌለም መታወቅና በኢህአዴግ በኩል መታመን ይኖርበታል።

60ኛ አመቱን አከበረ የተባለውና አቶ መለስን ለዚሁ ስብሰባ "ጋበዘ" የተባለው የመምህራን ማህበር ሁኔታ ለዚህ አባባሌ ማሳያ ኾኖ ሊቀርብ ይቻላል። ይህን ማኅበር እና አመራሩን የሚቀናቀን ሌላ ማኅበር እና ሌላ አመራር እንዳለ ይታወቃል፤ መምህሩ ከሁለቱ ማኅበራት እና አመራሮች መካከል የትኛው እንደሚወክለው በነጻነት ተወያይቶ ለመወሰን የሚያስችለው እድል እንዳለገኘም ይታወቃል። ይሁን እንጂ መምህሩ ባልመረጠበትና ባልወሰነበት ሁኔታ ኢህአዴግ ከመረጠለት እና ከወሰነለት ማኅበር ጋር ነው ውይይቱ የተደረገው። ይህ ደግሞ የአንድ ወገንን አቋም መስሚያ ከመሆን አልፎ ነጻ የብዙዮሽ ውይይት ሊካሄድበት አይችልም።

## <u>ትምህርትና ልማት</u>

ትምህርት ለወላጅም ለመንግሥትም ትልቅ የኢንቨስትመንት ውሳኔ ነው። አንድ ቤተሰብ ልጆቹን ለትምህርት ሲልክ በእንተ ነገ ብሎ የሚያወጣው ወጭ እና የሚሠዋው ጥቅም ይኖራል፤ መንግሥት ለትምህርት የሚመድበው የሃገር ሃብትም እንደዚሁ በእንተ ነገ ተብሎ የሚደረግ ነው። በኢንቨስትመንቱ መጨረሻ ላይ የሚወጣው ምርት ገበያ ላይ ቀርቦ፣ ገዢና ተጠቃሚ አፍርቶ፣ ለምርቱ ከወጣው ወጪ በላይ ጥቅም ማስገኘት እንዳለበት ሁሉ፤ በቤተ ሰብ እና በሃገር ሃብት የተማረው ዜጋም በሥራ አለም ውስጥ ተሠማርቶ ለማስተማርያው የወጣውን ሃብት ሊተካ የሚችል መኾን ይኖርበታል። ይህንን ማሳካት የሚቻለው የትምህርት ሥርዐቱ የአጠቃላይ አገራዊ ልማቱ አካል ሆኖ ሲጓዝ፤ ሁለቱም በአቅርቦት እና ጠቀሜታ መርሕ ሲተሳሰሩ ነው።

በአገራችን በርካታ ትምህርት ቤቶች ዩኒቨርስቲዎች ከመገንባታቸው በተጨማሪ የእነዚህ መሠረተ ልማት ግንባታዎች መኖር ለትምህርት አንደ ትልቅ ግብኣት መሆኑ አሌ የማይባል ነው። ይኹንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ፍሬ የሆነው ምሩቅ ወጣት ወደ ምርት እና አገልግሎት ሥራ ገብቶ በእርሱ ላይ የፈሰሰውን ሃብት ሊመልስ በሚችልበት ኹኔታ ላይ አይገኝም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የኢህአዴግ ፖሊሲ በትምህርትና በልማት መሃከል ሊኖር የሚገባው ቁርኝት በተጨባጭ ሊጠብቅ ባለመቻሉ ነው።

ይህ በፖሊሲና እና በልማት መካከል የታየው መፋለስ ቢያንስ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በኢህአዴግ ውስጥ ግንዛቤ እንዳገኘ አውቃለኹ። ‹‹ለምርጫ 1992 መርሃ ግብር ማዘጋጃ ሊሆን የሚችል ሌላው ቢቀር የማሕበረዊ እና የኢኮኖሚ ዘርፎች ግምገማ ለማደረግ እንችል እንደሆነ እንሞክር›› በሚል የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለውይይት መቀመጥ ጀምሮ ነበር። ግምገማው ‹‹በክልሎች ሪፖርት ይጀመር›› ተብሎ የክልል ፕሬዚዳንቶች ስለ ትምህርት ያቀረቡት ግምገማ አስደንጋጭ ነበር። በወቅቱ የክልል ትግራይ ፕሬዚዳንት የነበረው አቶ ገብሩ ዐስራት ስለዚሁ ሲገልፅ ‹‹የትምህርት ፖሊሲያችን ከዚህ በፊት ያላየናቸው ችግሮች አሉበት፤ ፖሊሲው ከአጠቃላይ ልማታችን ጋር ባለመያያዙ በጊዜ ሂደት የሚፈነዳ ፈንጂ (time bomb) እየጠበቀን ነው›› ነበር ያለው። ማህበራዊ እና ኢኮኖምያዊ ዘርፎቹን ለማየትም የግድ የፌዴራል መንግስት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ሪፖርት መቅረብ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ በዝያውም ላይ

ውስጣዊ ክፍፍሉ እና እልባት ያላገኘው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ስለነበረ በተረጋጋ ኹኔታ የተሟላ ግምገማ ሊደረግበት እንደሚገባ ተስማምተን ጉዳዩ በይደር ታልፏል። ከዚያ በኋላ የበላይ አመራሩ መሠነጣጠቅ ስለተከሰተ ምን እንደተደረገ አላውቅም።

በአሁኑ ወቅት የኢህአዴግ የትምህርት ፖሊሲ የተቀራኘው ከተጨባጩ የአገራችን ሁኔታ እና ከአጠቃላይ ልማታችን ጋር ሳይሆን የሚልየነም ግቦች ተብለው ከሚታወቁትና እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከሚመጣው የውጭ አገር መንግስታት እና የዓለም አቀፍ ተቋማት የገንዘብ ፍሰት ጋራ ነው፤ በክልሎች ያለው የአስተማሪዎች እና የትምህርቱ ይዞታ የሚያሳየውም ይህንኑ እውነታ ነው። አብዛኛዎቹ አስተማሪዎች የገዢው ፓርቲ አባል ናቸው። ይህንን ካልተቀበሉ የስራ ዋስትና የላቸውም። ስለ ትምህርቱ የሚሊኒየም ግብ ይነገራቸዋል፤ ይህንን የማሳካት ግዴታ እንዳለባቸውም ይገለጽላቸዋል።

ግቡን ማሳካት ካልተቻለ ለትምህርት የሚሆን የውጭ እርዳታ እንደማይገኝ፤ እርዳታው ካልተገኘ ደግሞ የትምህርት ባጀት እና ደመወዝ ብሎ ነገር እንደማይኖር ይነገራቸዋል። የሚሊየነም ግብ ተብሎ የተቀመጠውን የትምህርት ሽፋን ግብ ለሚሟላት ሲሉ ርእሰ መምህሩ እና አስተማሪዎች ማድረግ ከሚጠበቅባቸው ግዴታዎች አንዱ ትምህርት ቤት በሚከፈትበት ወቅት እንደምንም ብሎ ብዙ ተማሪዎች እንዲመዘገቡ ማድረግ ነው። ይህን ካሳኩ የትምህርት ሽፋን ይህን ያክል ፐርሰንት ደረሰ ይለፈፋል።

ከምዝገባው በኋላ ተማሪዎች ትምህርት መቀጠል አለመቀጠላቸው ያለው አሳሳቢነት ከሰው ሰው ሊለያይ ይችላል፤ ዋናው ጭንቀታቸው የሚኾነው ከተመዘገበው ተማሪ ስንቱ አለፈ? ስንቱስ ወደቀ? ላይ ነው። ‹‹የደገመ በዛ›› ቢባል ርእሰ መምህሩንና አስተማሪዎቹን ለትችት እና ግምገማ ይዳርጋል፤ በዝያውም የሚለየነም ግቡን ሊያፋልስ ስለሚችል ያለው አማራጭ ተማሪዎቹን በገፍ ወደ ሚቀጥለው ክፍል ማሳለፍ ይኾናል።

ወጣቱ በዚህ መልክ ይለፍ እየተባለ ዐሥረኛ ክፍል ይደርስና ብሄራዊው ፈተና እንደሚኾን ያደርገዋል፤ ከዚያም ተምሮ ወላጆቹን ይጦራል የተባለው ልጅ አሁን አጉል ሁኔታ ላይ ነው ወድቆ የሚገኘው፤ ወይ ከጧቱ ስራየ ብሎ የአባቱን እግር ተከትሎ የአባቱን ሙያ አልተለማመደ፤ ወይ ከዘመናዊው የትምህርት አለም ፋይዳ ያለው ክህሎት አላመጣ፤ ከሁለቱም ያጣ ዜጋ እየኾነ ነው።በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው ችግርም ከዚህ የተለየ አይኾንም። አንዲት የማውቃቸው እናት ስለ ተማሪዎች በገፍ ወደ ዩኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጆች አልፋችኋል መባል ሲገልፁልኝ ‹‹ወድቃችኋል በለው ጎዳና ላይ ከሚያፈሱዋቸው አልፋችኋል ብለው ዩኒቨርሲቲዎቹ ውስጥ ቢያቆዩዋቸው ይሻላቸዋል›› ያሉትን አስታውሳለኹ።

## ገደል የሚገባው ማን ነው?

አቶ መለስ ሰሞኑን ጋዜጣዊ መግላጫ በሰጠበት ወቅት የወ/ት ብርቱካን መታሰር ‹‹የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው›› የሚሉ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችን በሚመለከት ‹‹ቢፈልጉ ሊማሊሞን ማቋረጥ ይችላሉ እንጂ በአገራችን ጉዳይ እንዲገቡ አንፈቅድም›› ሲል ተደምጧል። አያይዞም ወ/ሪት ብርትኳን አድርጊ የተባለቸውን ያላደረገችው ‹‹የኢህአዴግ መንግስት የውጭ መንግስታትን ጫና ፈርቶ የማሰር እርምጃውን ከመውሰድ ይታቀባል የሚል የተሳሳት ግምት በመያዟ ነው›› ሲል ተሰምቷል።

‹‹ብትፈልግ ወደ ሊማሊሞ ገደል ግባ›› እየተባለ ያለው የዓለም አቀፍ ማኀሕበረ ሰብ በኢትዮጵያ ትምህርት ይስፋፋ ዘንድ የሚሊየነም ግቦችን ጥሎ ለዚሁ ስኬት ሃብት እያፈሰሰ ነው፤ ይህም የሚደገፍ ተግባር ነው። ‹‹በመንግስት ባጀት›› ተሠሩ እየተባለላቸው ያሉትን የትምህርት እና ሥልጠና ማእከላት መሠርያ ገንዘብ የሚመጣው

ከዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ እርዳታ መሆኑም አሌ የሚባል አይደለም። ኢትዮጵያ ለሚሊየነሙ የትምህርት ግቦች ተብሎ ዓለምአቀፉ ማኅበረ ሰብ ከሚቆርጥላት ገንዘብ ባንድ በኩል የውጭ ምንዛሪ ታገኛለች፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለትምህርት የሚኾን በቂ ባጀት ለመመደብ ይቻላታል። ይህ የውጭ ምንዛሪ በሃገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ያለው ስፍራ ምን ያህል ግዙፍ እንደ ኾነም ሁላችንም ልንገነዘበው የምንችል እውነታ ነው።

ባለንበት ዘመን ሰብአዊ ልማት እና ሰብአዊ መብት ተነጣጥለው የማይታዩ እውነታዎች ናቸው። ለሰብአዊ ልማት ሃብታቸውን የሚሰጡ ያሉት እና ለሰብአዊ መብት ጥበቃ የሚጮኹ ወገኖች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች እንደሆኑ ለአቶ መለስ መንገር አይኖርብኝም። እነዚህ ወገኖች በቀርጥ ገደል ግቡ መባላቸውን ሲያዉቁ ዶላሩ ይቀራል፤ ከዚያ በኋላ ገደል ውስጥ የሚገባው ማን እንደሚኾን ግን እነሱም እኛም እናውቃለን። ለነገሩ አቶ መለስ ይህንን የሚለው ለሃገር ውስጥ የፖለቲካ ፍጆታ ብሎ እንደሆነ እነሱም ሳይረዱለት አይቀሩም።

እንደ አውነቱ ከሆነ የ‹‹አንድነት›› ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ሊቀ መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚዲቅሳ አቶ መለስ ያለው ዓይነት ‹‹የተሳሳተ ግምት›› አልነበራትም። ይህንን ስል ግምቴን ማስቀመጤ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ፤ እውነተኛ ምስክርነቴን እንጂ። የሶስት ቀን ገደብ በተሰጣት በሁለተኛው ቀን አግኝቻታለኹ፤ አነጋግሬያታለኹም። በአካላዊ ነጻነቷ እና በህሊናዊ ነጻነቷ መካከል አንዱን ምረጭ እንደተባለች ገብቷታል፤ ኢህአዴግ የፈለገው *‹‹ለሁለተኛ ጊዜ አንበረክክን፤ ለሁለተኛ ጊዜ ይቅርታ አስጠየቅን›* ብሎ የብርቱካንን ክብር በምርኮ ለመውሰድ እንጂ ይቅርታ መጠየቅ አለመጠየቋን ለማረጋገጥ እንዳልኾነ ገብቷታል። ይህንንም ቃሌ በሚለው ፅሑፏ ገልጻዋለች።

ወ/ሪት ብርትኳን እንደምትታሰር ገምታ ነበር። እርሷ ራሷ ኢህአዴግ ለሰብአዊ መብት ያለውን ‹‹ቸርነት›› አሳምራ ሰለምታውቅ ‹‹ኢህአዴግ ለፈረንጆች ብሎ ይተወኛል›› የሚል ግምት አልነበራትም፤ ሊኖራትም አይችልም። እስር የሚያሳጣው ግዙፍ ሰብአዊ ዕሴት አለ፤ የአገር እና የኅሊና ነጻነት ጉዳይ ኾኖበት ካልኾነ በስተቀር ‹‹ፈረንጅ ይደርስልኛል›› ብሎ በዚህ ግዙፍ ዕሴት ላይ ቁማር የሚጫወት የኢትዮጵያ ፖለቲከኛ ይኖራል ብላቸኹ መገመታችኹ የቆማችኹበትን ስርዓት በሚገባ እንደማታውቁት ያስረግጣል። ኢህአዴግ ወ/ሪት ብርቱካንን ያሰራት ይህን ‹‹የተሳሳት ግምት›› ስለያዘች ነው ብሎ ለፈረንጆች በጄ እንደማይል ለማሳየት ከሆነ ተሳስቷል። እርምጃውን ዳግምኛ ሊመረምረው ይገባል እላለሁ።

የካቲት 28 ቀን 2001 ዓ.ም

<u>ማስታወሻ</u>

*ይህ ጽሑፍ የካቲት 28 ቀን በወጣው አዲስ ነገር ጋዜጣ ወጥቷል

**ስየ አብራሃን በ seabrag@gmail.com ማገኘት ይቻላል